# ማውጫ


ርዕስ ገጽ

I. መግቢያ .................................... 1

II. የፖሊሲው ዓላማዎች .................................... 2

III. ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች .................................... 2

1. የዱር እንስሳት ሀብት ልማትና ጥበቃ .................................... 2

1.1 የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎችን ስለማስተዳደር .................................... 2

1.2 በሀገሪቷ ብቻ የሚገኙና ቁጥራቸው ተመናምኖ ለአልቂት ሥጋት የተጋለጡ የዱር እንስሳትን ስለመንከባከብ.................................... 4

1.3 የዱር እንስሳት ሀብትን ከአደጋ ስለመከላከል.................................... 4

1.4 የዱር እንስሳት የጤና አገልግሎትን ስለማስፋፋት .................................... 5

1.5 የዱር እንስሳትንና ውጤቶቻቸውን ዝውውር ስለመቆጣጠር .................................... 5

1.6 ጉዳት የሚያደርሱ የዱር እንስሳትን ስለመቆጣጠር .................................... 6

2. የዱር እንስሳት ሀብት አጠቃቀም .................................... 6

2.1 የዱር እንስሳት የሚሰጡትን ጥቅም ስለመለየት .................................... 6

2.2 ኢኮ–ቱሪዝምን ስለማበረታታትና ስለማስፋፋት.................................... 7

2.3 የዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ውጤቶች ገበያ ስለማስፋፋት.................................... 7

2.4 ከዱር እንስሳት ሀብት ልማት ስለሚገኝ ገቢ አጠቃቀም.................................... 8

3. የባለሀብቶች ተሳትፎ .................................... 8

በዱር እንስሳት ሀብት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም ረገድ ባለሀብቶችን ስለማበረታታት .................................... 8

4. የዱር እንስሳት ጥናት፣ ትምህርትና ስልጠና ስለማካሄድ.................................... 9

4.1 የዱር እንስሳት ሀብት ጥናትን ስለማስፋፋትና ስለማጠናከር.................................... 9

4.2 ስለትምህርትና ስልጠና.................................... 10

5. ስለዱር እንስሳት ሀብት መረጃ.................................... 10

የዱር እንስሳትና የጥበቃ ቦታዎች መረጃ ሥርዓትን ስለመዘርጋት.. ... 11

IV. የፖሊሲው አፈፃፀም.................................... 11

# I. መግቢያ

ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ዓይነት የተፈጥሮ ውበት ያላቸው ብርቅ የሆኑ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ባለቤት ነች፡፡ ይህ ሀብቷ በሀገሪቱ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያደርግ እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ቢሆንም፣ ከንዑስ ክፍለ ኢኮኖሚው እስከአሁን ድረስ የሚጠበቀውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሳታገኝ ቆይታለች፡፡

ለዚህም ዋና ዋና ምክንያቶች ሆነው ከሚጠቀሱት መካከል አግባብነት በሌለው የመሬት አጠቃቀም መንስኤ በዱር እንስሳትና በመኖሪያ አካባቢያቸው ላይ የሚደርሰው ውድመት፣ ያልተመጣጠነ የሕዝብ ብዛት ዕድገት የሚፈጥረው ጫናና የሕገ–ወጥ ሰፈራ መስፋፋት፣ የሕገ–ወጥ አደንና እነዚህን የመሳሰሉት ምክንያቶች ሲሆኑ፣ ከዚህ የተነሳ የዱር እንስሳቱ እጅግ ለከፋ አደጋ ተጋልጠው ይገኛሉ፡፡

መንግሥት በሀገሪቱ የዱር እንስሳት ሀብት ላይ እየተባባሰ የመጣውን የእልቂት አደጋ ለመግታትና አገሪቱ ከሀብቷ ማግኘት የሚገባትን ኢኮኖሚያዊ (በቱሪዝም፣ በዱር እንስሳት በሕይወትና በውጤቶቻቸው ንግድ፣ በስፖርታዊ አደንና በመሳሰሉት) ጥቅም እንድታገኝ ለማድረግ ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታና አሁን ካለው ዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ መርህ አኳያ የተቃኘ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ አቅጣጫ መንደፍ ትኩረት የሚሰጠው አብይ ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ሀብት በተገቢው መንገድ ተጠብቆና ለምቶ አስፈላጊውን ጥቅም እንዲሰጥ፣ የዱር እንስሳቱና የተፈጥሮ ሀብት አካባቢው ተጠብቆና ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ፣ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከዱር እንስሳት ሀብት ልማትና አጠቃቀም በሚገኝ ገቢ ለማገዝ፣ በሀብቱ ላይ ያንዣበበውን አደጋ አስወግዶ ሕብረተሰቡን ያሳተፈ ዘላቂ ልማትና ዕድገት ለማምጣት እንዲቻልና ከዚህ በፊት የተገቡ ዓለም አቀፍ የዱር እንስሳት ስምምነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ፣ ፖሊሲና ስትራቴጂ ማውጣት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

የተዘጋጀው ፖሊሲና ስትራቴጂ ስለ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ፣ ስለ ዱር እንስሳት ሀብት አጠቃቀም፣ ስለሕብረተሰቡና የግል ባለሀብቶች ተሳታፊነት፣ በዚህ ረገድ መደረግ ስለሚኖርበት የግንዛቤ ማዳበሪያ ትምህርትና የመረጃ ሥርዓት የሚተነትን ሆኖ በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፡፡

## II. የፖሊሲው ዓላማዎች

የፖሊሲው ዋና ዓላማ በሀገራችን የዱር እንስሳትንና የመኖሪያ አካባቢያቸውን በዘላቂነት በመጠበቅና በማልማት የዱር እንስሳት ሀብት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቅበትን ድርሻ አበርክቶ ሕብረተሰቡን በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ለማድረግ ነው።

ዝርዝር የፖሊሲው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. የዱር እንስሳት ሀብትን በአግባቡ በመጠበቅ፣ በማልማትና በማስተዳደር ዘላቂና ውጤታማ በሆነ መንገድ የበኩሉን ኢኮኖሚያዊና ሥነ ምህዳራዊ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማድረግ፣
2. በዱር እንስሳት ዘርፍ አገሪቱ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፋዊ ሕጐችና ስምምነቶች መሠረት በማድረግ የዱር እንስሳቱንና የመኖሪያ አካባቢያቸውን የተፈጥሮ ሀብት በመጠበቅ የተፈጥሮ ሚዛን እንዳይዛባ ማድረግና በተጨማሪ ይህ ሀብት ተጠብቆና ለምቶ ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ፣

## III. ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች

### 1. <u>የዱር እንስሳት ሀብት ልማትና ጥበቃ</u>

### 1.1 የዱር እንስሳትንና የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎችን ስለማስተዳደር

<u>ፖሊሲ</u>

ብሔራዊ ፓርኮችና ሌሎች የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ሕጋዊ ሰውነት ኖሮአቸው የዓለም አቀፍ መርሆዎችንና ደረጃዎችን ጠብቀው የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ባረጋገጠ መልኩ በፌዴራል መንግስት፣ በክልሎች፣ በግል ባለሀብቶች እና በአከባቢ ሕብረተሰብ እንዲተዳደሩ ይደረጋል።

<u>ስትራቴጂዎች</u>

ሀ. ብሔራዊ ፓርኮችና ሌሎች የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች (የዱር እንስሳት ጥብቅ ክልል፣ የዱር እንስሳት መጠለያና የቁጥጥር አደን ቀበሌዎች) በጥናት ተለይተውና ተከልለው ሕጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ ማድረግ፣

ለ. ለዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ሕብረተሰቡን ባሳተፈና ተጠ ቃሚነታቸውን ባረጋገጠ መልኩ ዓለም አቀፍ መርሆዎችን

የተከተለ ማኔጅመንት ኘላን እንዲዘጋጅና እንደአስፈላጊነቱ እየተሻሻለ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣

ሐ. በማንኛውም የዱር እንስሳት ጥበቃና መዘዋወሪያ ቦታዎች ውስጥ የሚታቀዱና በእንስሳቱ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ የልማት እንቅስቃሴዎችን መቀነስ፣

መ. የአስተዳደሩንና የማኔጅመንቱን ኘላን ለመተግበር እንዲቻል አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ እንዲዘጋጅ ማድረግ፣

## ፖሊሲ

**ከጥበቃ ቦታዎች ውጭ የሚገኘው የዱር እንስሳት የሀብት መጠንና ሥርጭት ተጠንቶ በአግባቡ እንዲተዳደርና እንዲጠበቅ ይደረጋል።**

### ስትራቴጂዎች

ሀ. ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ ያሉትን የዱር እንስሳት ቦታዎች በማጥናት እንደአስፈላጊነቱ ወደ ጥብቅ ቦታነት ማሳደግ፣

ለ. ከዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ውጭ ያሉት የዱር እንስሳትና የመኖሪያ አካባቢያቸው የሚተዳደሩበትን ደንብና መመሪያ ማዘጋጀትና ሥራ ላይ ማዋል፣

ሐ. ሕብረተሰቡ ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ የዱር እንስሳት ቦታዎችን በባለቤትነት ይዞ በመጠበቅና በማልማት ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፣

## ፖሊሲ

**ከጐረቤት አገሮች ጋር አዋሳኝ በሆኑና የዱር እንስሳት በሚዘዋወሩባቸው ሥፍራዎች በዓለም አቀፋዊ የዱር እንስሳት ጥበቃ ሕግጋት መሠረት የተቋቋሙ የጥበቃ ቦታዎች እንዲጠናከሩና አዳዲሶች እንዲቋቋሙ ይደረጋል።**

### ስትራቴጂዎች

ሀ. ከጐረቤት ሀገሮች አዋሳኝ በሆኑ ቦታዎች የተቋቋሙትን የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ማጠናከር፣

ለ. የጥበቃ ቦታዎች በሌሉባቸውና በአዋሳኝ ሥፍራዎች የሚቋቋሙ የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ከጐረቤት ሀገሮች ጋር በቅንጅት እንዲቋቋሙ ማድረግ፣

ሐ. የዱር እንስሳት ወደ ጐረቤት ሀገሮች መፍለስን/መሰደድን ለመግታት የዱር እንስሳት በሚዘዋወሩባቸው ሥፍራዎች የጥበቃ ቦታዎች እንዲቋቋሙ ማድረግ፣

**በሀገሪቱ ብቻ የሚገኙና ቁጥራቸው ተመናምኖ ለአልቂት ሥጋት የተጋለጡ የዱር እንስሳትን ስለመንከባከብ፣**

**<u>ፖሊሲ</u>**

**በሀገሪቱ ውስጥ ብቻ ለሚገኙትና ቁጥራቸው ተመናምኖ በእልቂት ስጋት ላይ ላሉት የዱር እንስሳት ዝርያዎች ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ ይደረጋል።**

<u>ስትራቴጂዎች</u>

ሀ. በሀገራችን ብቻ የሚገኙ የዱር እንስሳት ዓይነት፣ ሥነ-ሕይወት፣ ዝርያ፣ ብዛት፣

ሥርጭትና የአኗኗር ሁኔታ እንዲጠኑና በዘቦታ እንዲጠበቁ ማድረግ፣

ለ. በሀገራችን ውስጥ በመጥፋት ላይ ለሚገኙ የዱር እንስሳት ዝርያዎች መመናመን ምክንያት የሆኑት ችግሮች በጥናት ተለይተው እንዲታወቁና ችግሮቹ የሚቀረፉበትን መፍትሄ መፈለግ፣

ሐ. በእልቂት ስጋት ላይ ያሉ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ምቹ ወደ ሆነ የጥበቃ ቦታዎች እንዲዛወሩ ወይም የኢዘቦታ ጥበቃ እንዲደረግላቸው የሚያስችል ሁኔታን ማመቻቸት፣

## የዱር እንስሳት ሀብትን ከአደጋ ስለመከላከል

**<u>ፖሊሲ</u>**

**የዱር እንስሳትን ከልዩ ልዩ አደጋዎች ለመታደግ የሚያስችል የዱር እንስሳት ሀብት ጥበቃ ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል።**

<u>ስትራቴጂዎች</u>

ሀ. የዱር እንስሳትን ከተፈጥሮና ከሰው ሰራሽ አደጋዎች እንዲጠበቁ ለማድረግ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት መዘርጋት፣

ለ. በዱር እንስሳት ሀብት ላይ የሚደርሱትን የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች አስቀድሞ ለመከላከልና ለመቀነስ የሚያስችል የቅድመ-ማስጠንቀቂያ ትንበያ ሥራ የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ ባሳተፈ መልኩ እንዲሠራ ማድረግ፣

ሐ. ከጐረቤት ሀገሮች ጋር በሚገናኙ ወሰኖች አካባቢ በዱር እንስሳት ላይ

የሚደርሱትን የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች አስቀድሞ ለመከላከል የቅድመ–ማስጠንቀቂያ የመረጃ ልውውጥ ስምምነት ማካሄድ፣

መ. በዱር እንስሳት ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን ለመከላከል ትረስት ፈንድ ማቋቋም፣ ችግሩ ከአቅም በላይ ሲሆን ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ማሳወቅና ድጋፍ እንዲገኝ ማድረግ፣

## የዱር እንስሳት የጤና አገልግሎትን ስለማስፋፋት

### ፖሊሲ

በጥበቃ ቦታዎችና ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ በሚገኙ የዱር እንስሳት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡

#### ስትራቴጂዎች

ሀ. በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ስለ ዱር እንስሳቱ የጤና ሁኔታ ጥናት ማድረግና አስፈላጊውን መረጃ መሰብሰብ፣

ለ. የዱር እንስሳትን ሊያጠቁ የሚችሉ በሽታዎችን ተሸካሚና አስተላላፊ እንስሳትን መቆጣጠር፣ የበሽታዎችንም ዓይነት ለመለየት፣ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ዓቅም መፍጠር፣

ሐ. በሀገሪቷ ወካይ በሆኑ የጥበቃ ቦታዎች የዱር እንስሳት የሕክምና ጣቢያዎች በማቋቋም በማቴሪያል፣ በሰው ኃይል፣ በዱር እንስሳት ሕክምና ቴክኖሎጂ እንዲሁም ፋይናንስ ተጠናክረው አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣

## የዱር እንስሳትንና ውጤቶቻቸውን ዝውውር ስለመቆጣጠር

### ፖሊሲ

የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው ዝውውር አግባብ ባለው መንገድ እንዲካሄድ ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

#### ስትራቴጂዎች

ሀ. የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው በሕገ–ወጥ መንገድ በሀገር ውስጥ እንዳይዘዋወሩና ያአግባብ ወደ ውጭም እንዳይወጡ ከአገር የመውጫና መግቢያ በሮች ላይ ቁጥጥር ማድረግ፣

ለ. በዱር እንስሳት አጠማመድ፣ በዱር እንስሳት መቆያ ሥፍራ ዝግጅትና ከቦታ ወደ ቦታ በሚወሰዱበት ጊዜ አሠራሩ ዓለም አቀፍ የእንስሳት ደህንነት መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሐ. ለስጋት የተጋለጡ የዱር እንስሳት ንግድ ዝውውር በአገሪቱና በዓለም አቀፍ ሕጐች መሠረት እንዲካሄድ ማድረግ፣

መ. የዱር እንስሳትና የእንስሳቱ ውጤቶች ለንግድም ሆነ በሌላ ምክንያት ከአገር ውጪ ወይም በአገር ውስጥ በሚዘዋወሩበት ጊዜ አስፈላጊው የኳራንቲን ደንብ መሟላቱን ማረጋገጥ፣

### 1.6 ጉዳት የሚያደርሱ የዱር እንስሳትን ስለመቆጣጠር

**<u>ፖሊሲ</u>**

**የዱር እንስሳት በሰው፣ በቤት እንስሳትና በሰብል ላይ ጉዳት በሚያደርሱበት ወቅት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል፡፡**

<u>ስትራቴጂዎች</u>

ሀ. የዱር እንስሳት በሰው፣በቤት እንስሳትና በሰብል ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ቅድመ-መከላከል እርምጃ መውሰድ፣

ለ. ጉዳት የሚያደርሱ የዱር አንስሳት ዓይነትና የጥፋቱን መጠን ማጥናትና ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስልት መንደፍ፣

## 2. የዱር እንስሳት ሀብት አጠቃቀም

### 2.1 የዱር እንስሳት የሚሰጡትን ጥቅም ስለመለየት

**<u>ፖሊሲ</u>**

**የዱር እንስሳት ሀብት በዘላቂነት ለቱሪዝም፣ ለአደን፣ ለንግድ፣ ለእርባታና ለምግብነት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡**

<u>ስትራቴጂዎች</u>

ሀ. በሀገሪቱ ያለውን የዱር እንስሳት ክምችት ለማወቅና የዘለቄታዊ አጠቃቀም ስልት ለመቀየስ የሚረዳ መረጃ ለማግኘት የዱር እንስሳት ቆጠራ ማካሄድ፣

ለ. በቁጥጥር የአደን ቀበሌና ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ ያሉትን የዱር እንስሳት ሥርጭት በማያዛባ መልኩ ለስፖርታዊ አደንና ሌሎች ጥቅሞች ማዋል፣

ሐ. ከዱር እንስሳት ሀብት የሚገኙትን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ለማጐልበት ወቅታዊ መመሪያዎችና መረጃዎች ተዘጋጅተው ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ማድረግ፣

## 2.2 ኢኮ–ቱሪዝምን ስለማበረታታትና ስለማስፋፋት

<u>ፖሊሲ</u>

የተፈጥሮ አካባቢንና የዱር እንስሳት ሀብትን በማይጐዳ መልኩ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የኢኮ–ቱሪዝም እንቅስቃሴ ይደረጋል።

<u>ስትራቴጂዎች</u>

ሀ. በሀገራችን ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ ኢኮ–ቱሪዝም እንቅስቃሴ እንዲጐለብትና እንዲስፋፋ ዘላቂነት ያለው ሥርዓት መዘርጋት፣

ለ. ኢኮ–ቱሪዝምን ለማጐልበትና ለማስፋፋት የሚያስችሉ የመሠረተ ልማት አውታሮች እንዲዘረጉ ማድረግ፣

ሐ. የቱሪዝም እንቅስቃሴ በዱር እንስሳትና የመኖሪያ አካባቢያቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድር ሕጐችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣

## 2.3 የዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ውጤቶችን ገበያ ስለማስፋፋት

<u>ፖሊሲ</u>

ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸውን ተፈላጊነት ለማሳደግና የሚገኘውንም ገቢ ለማጐልበት ውጤቶቹ የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲመረቱ ይደረጋል።

<u>ስትራቴጂዎች</u>

ሀ. ለገበያ የሚቀርቡ የዱር እንስሳት ውጤቶችን በጥራት ለማምረት የሚያስችሉ ልምዶችንና ዕውቀቶችን በፓኬጅ መልክ በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

ለ. የዱር እንስሳት ውጤቶችን ተፈላጊነት ለማጐልበትና ገቢውንም ለማሳደግ በሀገር ውስጥ ገበያዎች እንዲፈጠሩ ጥረት ማድረግ፣

ሐ. የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው በሚወጣላቸው የጥራት ደረጃ መሠረት ለገበያ ማቅረብ ይቻል ዘንድ ደንብ እንዲወጣ ማድረግ፣

ፖሊሲ

የዱር እንስሳት ንግድ ልውውጥን አስመልክቶ የወጡትና የሚወጡት ዓለም አቀፍ ሕጎችና ስምምነቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣

ስትራቴጂዎች

ሀ. የዱር እንስሳትን በሚመለከት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚወጡ የንግድ ልውውጥ ሕጎች የሀገሪቱን ጥቅም ከማስጠበቅ አኳያ ያላቸውን ጠቀሜታ እያጠኑ ተግባራዊ ማድረግ፣

ለ. በዱር እንስሳት ውጤቶች ንግድ ልውውጥ ረገድ የላቀ ውጤት ከአስመዘገቡ ሀገሮች ልምድና መረጃን መለዋወጥና ለሀገሪቷ በሚበጅ መልክ ተግባራዊ ማድረግ፣

## 2.4 ከዱር እንስሳት ሀብት ስለሚገኝ ገቢ አጠቃቀም

ፖሊሲ

ከዱር እንስሳት ሀብት የሚገኘው ገቢ ለአካባቢው ሕብረተሰብ ጥቅም፣ ለዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ተግባርና እንዲሁም ለአገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ እድገት እንዲውል ይደረጋል፡፡

ስትራቴጂዎች

ሀ. ከዱር እንስሳት ሃብት አጠቃቀም የሚገኘውን ገቢ የፌደራል መንግሥትና ክልሎች የሚጋሩበት መንገድ መቀየስ፣

ለ. በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አካባቢ ለሚኖረው ሕብረተሰብ የተለያዩ የሥራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ ማድረግ፣

# 3. የባለሀብቶች ተሳትፎ

## 3.1. በዱር እንስሳት ሀብት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም ባለሀብቶችን ስለማበረታታት፣

ፖሊሲ

ባለሀብቶች በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር እንዲሳተፉ እንዲሁም በዘመናዊ የዱር እንስሳት አጠቃቀም ዘዴ በኤክስፖርት ላይ ያተኮሩ የዱር እንስሳት ውጤቶችን እንዲያመርቱ ድጋፍ ይሰጣቸዋል፡፡

ስትራቴጂዎች

ሀ. ባለሀብቶች የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን በሊዝ ወይም በኮንሴሽን በመያዝ በዱር እንስሳት አስተዳደር፣ ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም እንዲሳተፉ ማድረግ፣

ለ. ባለሀብቶች ጥራታቸውን የጠበቁ የዱር እንስሳት ውጤቶችን እንዲያመርቱ ድጋፍና መረጃ እንዲያኙ ማድረግ፣

ሐ. ባለሀብቶች ጥራት ያላቸው የዱር እንስሳት ውጤቶችን ለገበያ ለማቅረብ የሚያስችሉ ፓኬጆችን ማዘጋጀትና ስለአተገባበራቸው የስልጠናና የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፣

## 4. የዱር እንስሳት ጥናት፣ ትምህርትና ሥልጠና ስለማካሄድ

### 4.1 የዱር እንስሳት ሀብት ጥናትን ስለማጠናከር

ፖሊሲ

**የዱር እንስሳትና የመኖሪያ አካባቢያቸውን በዘላቂነት ለመጠበቅ፣ ለማልማትና ለመጠ ቀም የሚያግዙ ጥናቶች እንዲካሄዱ ይደረጋል።**

ስትራቴጂዎች

ሀ. በጥበቃ ቦታዎችና ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ ያሉ የዱር እንስሳትና የመኖሪያ አካባቢያቸው እንዲጠኑ፣ እንዲታወቁና እንዲለዩ ማድረግ፣

ለ. የዱር እንስሳትን የመኖሪያ አካባቢዎች በተመለከተ መረጃ መሰብሰብ፣

ሐ. በዕርባታ ወይም በይዞታ ሥር የሚገኙ የዱር እንስሳትን ሥነ–ሕይወትና ጤና በማጥናት አያያዛቸውን ማሻሻል።

ፖሊሲ

**ጠቃሚ የሆኑ ሀገር በቀል የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ዕውቀቶችና ልምዶች እንዲጐለብቱና በጥናት እየተሻሻሉ በስፋት እንዲተገበሩ ይደረጋል።**

ስትራቴጂ

ሀገር በቀል የዱር እንስሳት እውቀቶችና ልምዶችን በመለየት፣ በማሻሻልና ተስማሚነታቸውን በማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

## ፖሊሲ

ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የልምድ ልውውጥ ግንኙነቶችን በማጠናከር ተስማሚ የሆነ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ቴክኖሎጂ ሥርፀት እንዲኖለብትና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ተገቢው ትኩረት ይሰጣል፡፡

### ስትራቴጂዎች

ሀ. ተስማሚነታቸው የተረጋገጠላቸውን የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ቴክኖሎጂዎች ከውጭ ወደ አገር ውስጥ በማስገባት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

ለ. በቴክኖሎጂ ልውውጥ ረገድ በአንጻሩም በሀገሪቱ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ በጥብቅ ለመቆጣጠር የሚያስችል የቁጥጥር ሥልት መዘርጋት፣

## 4.2 ስለትምህርትና ስልጠና

### ፖሊሲ

ሕብረተሰቡ ስለዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ያለውን ዕውቀት ለማዳበር ቀጣይነት ያለው ትምህርትና ስልጠና ይሰጣል፡፡

### ስትራቴጂዎች

ሀ. ትምህርታዊ ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ሕብረተሰቡ ስለዱር እንስሳት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያለው ግንዛቤ እንዲዳብርና ለጥበቃው የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ማድረግ፣

ለ. የዱር እንስሳት ጥፋት ከማድረሳቸው በፊት የቅድመ መከላከል ስልት መቀየስና ስልጠና በመስጠት መተግበር፣

ሐ. የዱር እንስሳት ሊያደርሱ የሚችሉትን ጥፋት፣ እንዲሁም ጉዳት አድርሰው ሲገኙ መወሰድ ስለሚገባው ርምጃ ለሕብረተሰቡ ትምህርት እንዲሰጥ ማድረግ፣

መ. ስለዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው ንግድ የወጡትን ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ሕጐችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተዛማጅ የግልና የመንግሥት መ/ቤቶች እንዲያውቁትና እንዲተገብሩ ማድረግ፣

ፖሊሲ

የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን በዘላቂነት ለመምራትና ለማስተዳደር የሰው ኃይል ግንባታ እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

ስትራቴጂዎች

ሀ. በሀገራችን በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ረገድ በብቃት የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የሚያስችል አቅም መፍጠር፣

ለ. በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ት/ቤቶችና የማሰልጠኛ ተቋማት ስለዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም በሥርዓተ–ትምህርታቸው ውስጥ እንዲያካትቱ ማድረግ፣

## 5. የዱር እንስሳት ሀብት መረጃ

### 5.1. የዱር እንስሳትና የጥበቃ ቦታዎች መረጃ ሥርዓትን ስለመዘርጋት

ፖሊሲ

በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ላይ ያተኮረ ወቅታዊ የሆነ የመረጃ አሰባሰብ፣ ቅንብርና ሥርጭት ሥርዓት በመዘርጋት ተገቢው አገልግሎት ለተጠቃሚው እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

ስትራቴጂዎች

ሀ. የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የመረጃ አውታር በማቋቋምና በማደራጀት ጥቅም ላይ ማዋል፣

ለ. መረጃዎችን በመተንተን እንደተጠቃሚው ዓይነትና ፍላጐት ተለይቶ እንዲቀርብ ማድረግ፣

ፖሊሲ

የዱር እንስሳት የመረጃ ሥርዓት ልውውጥና ቅብብሎሽ በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ መዋቅሮች ቅንጅት ላይ የተመሠረቱ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

ስትራቴጂዎች

ሀ. ተጠቃሚዎች የዱር እንስሳትን በተመለከተ የሚወጡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎችን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች እንዲያገኙ ማድረግ፣

ለ. የመረጃ ልውውጥ ዘዴዎች ቅንጅት ባለው መልክ እንዲካሄድ የሚያስችሉና ደረጃቸውን የጠበቁ የመረጃ መለዋወጫ ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

## IV. የፖሊሲው አፈፃፀም

1. ይህን ፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረት በማድረግ ክልላዊ መስተዳድሮች የራሳቸውን የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ፖሊሲና ስትራቴጂ ማዘጋጀት ይችላሉ።
2. የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ይህን የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ፖሊሲና ስትራቴጂ በሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ መዋቅሮች እንዲደራጁ ያደርጋል፣ ልዩ ልዩ ኘሮግራሞችንና ኘሮጀክቶችን ይነድፋል፣ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ያወጣል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል።
3. ይህ የዱር እንስሳት ሀብት ልማትና ጥበቃ ፖሊሲና ስትራቴጂ በየወቅቱ የሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ውጤት እየተገመገመ አስፈላጊ በሆነበት ወቅት ሊሻሻልና ሊለወጥ ይችላል።